# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና
ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም።

ቁጥር 15 ቀን 17/ 3/ 67.

## ታሪክን የሚያጎድፍ ፋሽስታዊ ድርጊት

ቅዳሜ ህዳር 14 ቀን ማታ ወታደራዊው መንግስት 60 ሰዎችን ያለበቂ ምክንያት መረሸኑ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የውጭ ተመልካቾችን ጭምር ግራ አጋብቶአቸዋል። ምንም እንኳን እስካሁን ለደርጉ ያለቅጥ መርበትበት ምክንያት የሆነው ጉዳይ በግልጽ ባይታየንም ድርጊቱ ከመርበትበት የተነሳ የተፈፀመ መሆኑን ደርሰንበታል። ከኢትዮጵያም ሆነ ከአለም ሕዝብ በጣም ከፍ ያለ ቁጣን አስከትሎአል፤ የደርጉን ደጋፊዎች እንኳን ሳይቀር አሸብሮአቸዋል። ደርጉ በቃል በሚሰብከውና በድርጊት በሚፈጽመው መካከል ትልቅ ትራኔ መኖሩን ግልጥልጥ አድርጉታል።

የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ከሁሉም ያስገረመውና ያስቆጣው በአቋማቸውና በህይወት ታሪካቸው የተለያዩ፡ሕዝቡን ሲበድሉና ሲያሰቃዩ የኖሩ አድሃሪዎችና ሲታገሉለት የነበሩትን ተራማጆች በአንድነት ጠቅልለው እንደበግ መፍጀታቸውና ያለአንዳች የቀብር ስነስርአት መጣላቸው ነው። በዚህች በማተረሳ ምሽት የተረሸኑትን ሰዎች በጠቅላላው አሰስት ላይ ከፍሎ ማየት ያስፈልጋል።

በአንደኛው ክፍል የቀድሞው ንጉስ አሽከሮችና ባለሟሎች ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የበደሉና የበዘበዙ፡ብዙ ግፍ የፈፀሙ የፊውዳሉ ስርአት/ምሰሶዎች ነበሩ። ስለዚህ በስልጣን ላይ ሆነው በጣም አደገኞች በነበሩበትና ደርጉን ለመገልበጥ ያሰጋ በነበሩበት ጊዜ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች የፖለቲካ እርምጃ እንዲወሰድባቸው መጠየቃቸው ይታወሳል። ሆኖም የፖለቲካ እርምጃ ሲባል የህዳር 14 ቀኑን አይነት ፋሽስታዊ ፍጅት መጠየቃቸው አልነበረም። በመሰረቱ ሰፊውን ሕዝብ በበደሉ ሰዎች ላይ የፖለቲካ እርምጃ ሲወሰድ በአስቸኳይ ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ተቋቁሞ፡ የሰዎቹ ጉዳይ በክፍት/በግልጥ/ችሎት ታይቶ ይፈረድባቸውና ቅጣቱም ወዲያውኑ ይፈፀማል ማለት ነው። እንደየሁኔታው በሞትም ሆነ በእስራት የሚቀጣ ወይንም በነፃ የሚለቀቅ ይኖራል። ይህ አሰራር ሰፊው ሕዝብ ፍርዱ ለምን እንደተሰጠ በግልጽ አውቆ ትምህርት እንዲያገኝበት ይረዳዋል። በተጨማሪም በማናቸውም ሰው ላይ የሞትም ሆነ ሌላ አይነት ቅጣት ሲደርስ ተገቢ መሆኑ ለሁሉም በግልጽ ስለሚታይ የተመልካቹ ህሊና አይረበሽም።

ህዳር 14 ቀን በተረሸኑት ሰዎች ላይ የተፈፀመው ድርጊት ግን ከዚህ የተለየ፡ በዳኝነት ታይቶ ፍርድ ያልተሰጠበት፡ የሰውን ህሊና የሚያሸብር ፋሽስታዊ ፍጅት ነበር። በብዙ ምክንያቶች ሊነቀፍ ይገባል። አንደኛ ነገር፡— ደርጉ ራሱ 'ለሁሉም ፍትህ መስጠት አለብን' በማለት ጉዳዮን በመርማሪ ኮሚሽን ሲያስጠናና ከቆየና ውሳኔ የሚሰጥ የጦር ፍርድ ቤት ካቋቋመ በኋላ፡ጉዳዮን በክፍት ችሎት በማስፈረድና ለሕዝቡ ተገቢውን ትምህርት በማበርከት ፈንታ እስረኞችን ቶር በሚያሰኝ አኳኋን ያለፍርድ ረሸናቸው። ሁለተኛ ነገር፡— የሟቾቹ አመራረጥ ጉዳይ ትክክል አይደለም። የስርአቱ ቁንጮ አጤ ሃይለስላሴ በክብር ተይዘው በቤተመንግስት ሲቀመጡ አሽከሮቻቸውን ያለፍርድ መረሸን ምን ይባላል? ደግሞስ ከታሰሩት ባለስልጣኖች መካከል እነዚህ የተረሸኑት በተለይ የተመረጡበትን ምክንያት የሚያሳይ ምንም ነገር የለም። ሶስተኛው ነቀፌታ ደግሞ ሰብአዊ ስሜትን የሚመለከት ነው። የእነዚህ የቀድሞ ባለስልጣኖች ጥፋት ምንም እንኳ በግልጥ ቢታወቅ በእስር ቤት ሆነው ፍርዳቸውን ሲጠባበቁ ፍርዱን ሰርዞ እንደከብት ነድቶ መረሸን ሰብአዊ ስሜትን የሚነካ የአረመኔ ተግባር ነው።

ከሞቱት ሰዎች መካከል በሁለተኛው ክፍል ሌተና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ይገኛሉ። ደርጉ ጄኔራሉን መረሸኑን አውጆ ነበር፤ ነገር ግን ተረቱን ማንም ስላልተቀበለለት ጦርነት ከገጠሙና ብዙ ከተዋጉ በኋላ መሞታቸውን ማመን ግድ ሆኖበታል። እንዲያውም የቀሩት 59 ሰዎች የተረሸኑት ጄኔራሉ ስለሞቱ ነው። የጄኔራሉን ሞት ሕዝቡ ሲሰማ ትልቅ ተቃውሞ እንደሚነሳ በመገመት ሌሎች ሰዎችን ረሽኖ ሕዝቡን ለማወናበድና ስሜቱን ለመከፋፈል የታቀደ ይመስላል።

ሌ/ጄኔራል አማን ከዚህ በፊት ደርጉን በመወከል በወሰዱአቸው ፀረ ሕዝብ እርምጃ ዎች ምክንያት፤በተለይም በአደረጉአቸው ዲስኩሮች በኤርትራ የነፃነት ተዋጊያችና በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ላይ ደጋግመው በመዛታቸው፤ ከተራማጆቹ ብዙ ወቀሳና ተቃውሞ ተሰንዝሮባቸው ነበር:: ነገር ግን ወደኋላ የራሳቸውንና የደርጉን ጥፋት ስለተገነዘቡ፤ራሳቸውንም ሆነ ደርጉን ለማረም እንደሞከሩ አሁን ተረጋግጧል::ይህ ሙከራቸውም እንደጥፋቱ ተቆጥሮ ለሞት እንዳበቃቸው ማወቅ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ነው::

በውጭ የዜና ምንጮች እንደተነገረውና ከሚታመኑ የአገር ውስጥም ምንጮች እንደታወቀ ው በደርጉና በጄኔራሉ መካከል ልዩነትን ካስነሱ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:—

1. ወታደራዊውን መንግሥት የሚመሩት ሰዎች የጦር እንጂ በቂ የፖሊቲካ እውቀት እንደሌላቸው በማመልከት፤ከሲቪልና ከወታደር የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ጄኔራሉ ማሳሰባቸው፤
2. የኤርትራና ሌሎችም የብሔሮች ጉዳይ ሊፈታ የሚችለው በሰላም መንገድ እንጂ በጦርነት ስለመሆኑን በማመልከት፤ደርጉ ይህን ፕሮብሌም በኃይል ለመፍታት ከሚያደርገው ከንቱ ሙከራ እንዲቆጠብ ማስጠንቀቃቸው፤
3. በቂ ዝግጅት አለመደረጉን በማመልከት፤ "ዕድገት በኅብረት" በሚለው ፕሮግራም ተማሪዎችን ወደ ገጠር የመላኩ ጉዳይ እንዲዘገይ ማሳሰባቸው፤

እንደምናየው እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ የሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው::ደርጉ የጄኔራሉን አርአያ ተከትሎ በመታረም ፈንታ ጄኔራሉን አስሮና ማስገደሉ በጥብቅ ሊኮነን የሚገባው ፋሺስታዊ ድርጊት ነው::ደርጉ እንደተናገረውና የራሱና የኢትዮጵያ በሙሉ ጠሪ የነበረትን ጄኔራል ከአፉ ሀሪያች ጋር በአንድነት በማስገደሉ፤የኢትዮጵያንም ሆነ የዓለምን ሕዝብ አስገርሞታል::አጭበርባሪነቱን፤አወናባጅነቱንና ወስላታነቱን በይፋ አስመስክሯል::በፊት በመታለል ይደግፉት የነበሩትም የዋህ ሰዎች አሁን ድጋፋቸውን ነስተውታል::

ትናንት ማታ ከተረሸኑት ሰዎች መካከል በሶስተኛው ክፍል ውስጥ ወታደራዊ አምባገነንነትን የተቃወሙና ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም የጠየቁ የሰራዊቱ አባሎች፤እነ ሻንበል ደምሴ ሽፈራው፤ሻንበል በላይ ፀጋዬ፤ ሻንበል ወ/ዮሐንስ ዘርጋው፤ምክትል የአስር አለቃ ተክሌ ኃይሉ፣ ተራ ወታደር በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ፤የመቶ አለቃ ተስፋዬ ተክሌ፤ጁኒየር አክማን ዮሐንስ፡ ፍትዊና ኮሎኔል ደገዘ ይመኑ ይገኛሉ::እነዚህ የሰፊው ሕዝብ አርበኞች እንኳን መረሸንና ፈጽሞ መታሰርም አልነበረባቸው ግልጸ ነው:: እንደነዚህ ያሉትን የሰፊው ሕዝብ ወገኖች የሚረሽኑ እንደነሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ያሉ፤ደም የጠማቸው ፋሽስታዊ ወንበዴዎች ብቻ ናቸው::ፋሽስታዊው ደርግ ለነዚህ የሕዝብ አርበኞች ሕይወት በቀጥታ ተጠያቂ ነው:: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ግዳጃቸውን በትክክል በመፈጸማቸው በወንበዴዎች ለተሰውት ለነዚህ ሰማዕታት ሞት የሚበቀልበት ጊዜ ሩቅ አይደለም:: የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ጋዜጣ ለነዚህ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ቤተሰቦችና ዘመዶች ጥልቅ ኀዘኑን ይገልጻል::

ባለፈው ቅዳሜ የፈጸመውን ፋሽስታዊ ድርጊት ለሕዝብ ሲያውጅ፤ደርጉ ለግረ መንግሥቱን "በስራ መዘፍ" እያመካኘ የሚጠላቸውን ንጹሕ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከየመስሪያ ቤቱ እየጎተተ ለመረሸን እንደሚያስብ ያላንዳች ሀፍረት ገልጾ ነበር፤በውነቱ በዚህ አኳኋን የሚዘቱ ምንም ሕግ የማያውቅ የወንበዴዎች ድርጊት ብቻ ነው:: "ጀርመን ትቅደም" በማለት የመጀመሪያውን ፋሽስታዊ መርሀ በመፍጠር ለነ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ምሳሌ የሆኑት እነ ሂትለር እንኳን ለሰፊው ሕዝብ የነበራቸውን ንቀትና ጥላቻ ይህን ያህል ደፍረው በግልጽ አሳይተው ይሆን?

ባለፈው ቅዳሜ፤ ኅዳር 14 ቀን የደርጉ ፋሽስታዊ ድርጊት አስፈላጊውን ትምህርት መውሰድና ተገቢውን መደምደሚያ መስጠት ያስፈልጋል:: ይህ ፋሽስታዊ ድርጊት በደርጉ ውስጥ አንዳንዶች ስልጣን የጠማቸው ግለሰቦች ስልጣን መያዛቸውንና የዲሞክራሲው አሰራር በጭራሽ ማክተሙን፤ደርጉ ወደፍጹም የወንበዴዎች ድርጅት መለወጡን ያመለክታል::በድርጊቱ አስቀድሞ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ተደርጎ ከደርጉ አባሎች ብዙኃኑ ተስማምተውበት ነበር ለማለት እንዴት ይቻላል? ፍጹም ደርጉ ከሰፊው

ሕዝብ ራሱን በመነጠሉና ድጋፍ በማጣቱ ሥራ ከመሰሪያው በስተቀር ማንንም እንደማያምን ያሳያል:: ስለዚህ ክሽ ባለ ቁጥር በርግጥ እሽጋን በየአቅጣጫው እንደምትረጭ ኗርት፣ትንሽ የሀሳብ ልዩነት በተነሳ ቁጥር ታንኩን በየአቅጣጫው ለማሰማራትና በ.. በሕፃኑም ላይ ሳንጃውን ለመምዘዝ አገሪቱን በደም ጉርፍ ለማጥለቅለቅ መዘጋጀቱን ያሳያል:: በተጨማሪም ከዚህ በፊት በዚህ ጋዜጣ እንደተመለከተው የደርጉ ድርጊቶች አገሪቱን በሙሉ ወደ እርስበርስ ጦርነት በፍጥነት በማምራት ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል::ከዚህ ችግር ለመላቀቅ የሚቻለው ሰፊው ሕዝብ ድርጅቱን አጠንክሮ ትግሉን ካሰፋና ከአፋፋመ ብቻ ነው::<u>ለዚህም ግብ ተራማጅ ኃይሎችና ድርጅቶች በሙሉ ተግባራቸውን ማስተባበር ይገባቸዋል</u>:

ከዚህ ቀደም "ያለ ምንም ደም" እየተባለ ጆሮአችንን ሲያድነቁር የነበረው ለፊፋ ደርጉ ደም የተጠማ የፋሽስት ወንበዴዎች ድርጅት መሆኑ ለመሸፈን የታሰበ መሆኑ አሁን ለሁሉም በግልጽ ታይቷል::

የደርጉ መሪ ፣ የኢትዮጵያው አደልፍ ሂትለር፣ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባለፈው ሳምንት "የደርጉ አባሎች በሙሉ አስተዋዮች፣ቆራጦች፣ፈጣኖችና ተራማጆች ናቸው::.....፣ ....በተራመዱ ቁጥር የሚረግጡትን ምድር በጥንቃቄ እያስተዋሉ ነው::" "እንቅስቃሴያችንም "ኢትዮጵያውያኖችን ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያኖችንንም ያኮራና ዓለምን ያስደነቀ ነው፤ይ....ይህ ለውጥ.. የዓለምን ሊቃውንትን ምርምር ውስጥ አድርጉታል::"እያለ እራሱን ሲያሻሽጥ ነበር::

እንዲህ ያለ እውቀትና ጥንቃቄ የት ይገኛል! የትም ታይቶ ይታወቃል! አንድ እውነቱ ቢኖር የሻለቃው አሻንጉሊት የሆነው ደርግ በፋሽስታዊ ጭካኔው የዓለምን ሕዝብ አስደንቋል:: የአፍሪካ አገሮች ጋዜጦች የቀዳሚውን ምሽት ..ርሼና "የአፍሪካን ታሪክ የሚያጉድፍ ፋሽስታዊ ድርጊት" ብለው ሲሰይሙት፣በአረመኔነታቸው የታወቁት የነሻለቃ መንግሥቱ የምስጢር ወዳጆች፣የአሜሪካን እምፔሪያሊስቶች እንኳን በድርጊቱ በጣም ስለአፈሩበት "ለኢትዮጵያ ስንሰጥ የነበረውን ማንኛውንም ዓይነት እርዳታ አቋርጠናል" ብለው ለማወጅ ተገደዋል::

ፋሽስታዊ ወታደራዊ መንግሥት ይውደም

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይደራጅ

ተራማጅ ኃይሎች የትግል አንድነታቸውን ያጠንክሩ::

## ለፋሽስታዊ ጧስት አንንበረከክም፣

## ትግሉ እየተፋፋመ ነው።

1. የኅብረተሰብ ታሪክ ተመሳሳይነት፡

የሰውን ልጅ ታሪክ ዘር ብለን ስንመለከተው በእርግጥ በህግ የሚመራ መሆኑን እንረዳለን። ህግጋቱ ከሰው ፍጥረት፡ከሁኔታው፡ከፍላጐቱ፡ለመኖርና ለመሻሻል ከሚያደርገው ጥረትና ትግል የሚመነጩ ናቸው፣ የህይወት ትግል ህግጋት ናቸው። አንድ ሰው አንድ ነገር ሲያደርግ አንድ ነገር ይከተላል፣ ትንሽም ቢሆን ቅስቃሴ ከተደረገ ውጤት ወይም ተከታይ እንዳለው የማያከራክር እውነት ነው።

የህብረተሰብ ታሪክ በመሰረቱ ተመሳሳይና አንድም ነው ለማለት ይቻላል። ህግጋቱ፡ ስርአቱ እንደየስፍራውና ሁኔታው ምንም እንኳን አንዳንድ ለየት ያሉ ነገሮች ቢኖሩአቸውም ያው በአጠቃላይ አንድ ናቸው። ከልዩነቱ ይልቅ ተመሳሳይነቱና አንድነቱ እጅግ በጣም ጉልህ ነው።

በየትም አገር ቢሆን የሕዝብ እንቅስቃሴ ይደረጋል፣ የተጨቆኑና የተበዘበዙ የህብረተሰቡ መደቦች ወይም ክፍሎች ዘወትር ይህንን ሁኔታ ደስ ብሎአቸው አይቀበሉትም፣ ገዥዎቻቸውን ለማስወገድና ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት፡የድካማቸውን ፍሬ ለራሳቸው ጥቅም ለማድረግ ይፍጨረጨራሉ፣ ጫንቃቸውን የገሸለጠውንና ያቆሰለውን የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበር ሰባብረው ለመጣል ዝንተአለም የማያቋርጥ ትግል ያደርጋሉ። እኛም አሁን ያለንበት ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም።

ጊዜ ያነሳቸው አምባገነኖች ሕዝቡን አላዋቂ በማድረግ፣ እንዲያውም ምን ያውቃል፡ ደንቆሮ ነው፣ አይኑን ገና አልከፈተም፣ብልጣብልጦች ያወናብዱታል፣ እኛ ነን አሳቢው፣ ያለእኛ ምን አለኝታ አለው. እኛ ከተውነው ገደል ይገባል፣ ዘመቻ አድርገን እናስተምረዋለን፣ የታወረውን አይኑን እንከፍተለታለን፣ እስከዚያ ድረስ /ጊዜው አብዛኛውን ጊዜ አይነገርም፣ እንዲያው በደፈናው ይተዋል፣ አድርባይ ተለማማጮች 3:5:10 አመት ወዘተ. በማለት ፍርፋሪ ይለምኑበታል/ በእኛ ሞግዚትነት ይተዳደራል፣ እኛ ሕዝቡ ነን:ሕዝቡ እኛ ነው፣ ይህንን የሚቃወም የሕዝብ ጠላት ነው፣ ይውደም፣ በሞት እንቀጣዋለን ወዘተ. የሚባለው ሁሉ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ነው።

በኢትዮጵያም ነገሩ ያው ነው፣ በፊትም የነበረው ሁኔታ ሌሎች ብዙ አገሮች ያለፉበትን ይመስላል። አጤ ሃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ላይ ከባድ ግፍ እንደሰራ ሁሉ በሌሎችም አገሮች ቢጤዎቹ ተመሳሳይ ወንጀል ፈጽመዋል፣ በስልጣን ላይ አንሰራፍቶ ለመቆየት የመጨቆኛና የመደምሰሻ መሳሪያ —ሰላይ:ፖሊስ:ወታደር:ወዘተ.— አደራጅቶ ሰፊውን ሕዝብ ያስጨቁንና ያስመዘብር እንደነበረ ሁሉ በሌሎችም አገሮች እንደዚሁ አይነት ድርጊቶች ተፈጽመዋል።

ከየካቲት 66 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለውም እንቅስቃሴ በሌሎች አገሮች ከተደረጉት ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አለው። ሰፊው ሕዝብ የትግሉ አንቀሳቃሽና ባለቤት ሆኖ ሳለ በሃይለሥላሴ ከባድ ጭቆና ምክንያት በሚገባ ባለመደራጀቱና ባለመጠናከሩ ወታደሩ ቅድሚያውን ያዘ፣ እነአንዳልካቸውን የመሰሉ አጭበርባሪዎች ወታደሩን በገንዘብና በሹመት በመደለል ስልጣን ኮርቻ ላይ ወጥተው ለመቻቸት ሲጥሩ ሰፊው ሕዝብ ባለው የትግል መሳሪያና ዘዴ ስለተቃወማቸው በመወገዳቸው ሌሎች የቀበሮ ባህታዊያች መጡ፣ የድሃ ወገኖች ነን፣ ከሰፊው ሕዝብ ጉያ የወጣን ነን፣ ጨቋኞችንና በዝባዦችን ለማጥፋትና ሰፊውን ሕዝብ ለመበቀል ተመርጠን የመጣን ነን የሚሉ ጥቂት መኮንኖች አስልጣን ላይ ቂብ አሉ።ከሰፊው ሕዝብ ትከሻ ላይ ወጥተን እንደላደላለን ሲሉ ከሕዝብ ወገኖችና ከሰፊው ሕዝብ ተቃውሞ ገጠማቸው፣ ዛቻና ማስፈራራት የጥላቀላቀውን የባዶ ቃላት ከበሮ በሞኖፖል በያዙት ዜና ማሰራጪ ይደልቁት ጀመር። ብዙ ጣሩ፣ ብዙ ደከሙ፣ ውጤቱ እምብዛም አልተሳካም፣ ተቃውሞው፡ማጋለጡ ቀጠለ፣ በሃሳም መበሳጨት፡መቆጣት፡ማሰር፡መግደል፡እርስበርስ መባላት መጣ። ይህ ሁሉ 'የሊቃውንትን ምርምር'እንደማያከሽፈው ተረዱት፣ በሌሎች አገሮች የተደረገና የሚደረግም ነውና። የትግሉ እንቅስቃሴ ከሰር እየገፋ በመምጣቱ ድንጋጤ:ብርክ ያዛቸው፣ ህሊናቸውን በመሳት

በደመነፍስ ራሳቸውን ከትግሉ እንቅስቃሴ ሞገድ ለማዳን የባጡን የቆጡን መቧጠጥ ጀመሩ::

ታዲያስ ስልጣን ያስከራቸው ጥቂቶቹ ቢረኞች ሰሞኑን የአወጇአቸው ፋሽስታዊ ህጎች የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ የትግል ማእበል ምን ያህል ሊያግዱትና ሊገቱት ይችላሉ?

2. የህጎቹ ይዘት:

የፋሽስታዊ ህጎቹ ይዘትና አላማ እነአደልፍ ሂትለር:እነቤኒቶ ሙሶሊኒ አውጀዋቸው ከነበረት:ዛሬም እነቮርስተርና እነእያን ስሚዝ በደቡብ አፍሪካና በሮዴሽያ ከሚጠቀሙባቸው ጨቋኝና ፀረሕዝብ ህጎች ብዙ የሚለዩ አይደሉም:: መሰረተሃሳባቸውና አብዛኞቹም አናቅጽ እነዚህ የፋሽዝም ቀንደኞች ይጠቀሙባቸው ከነበረት ህጎች የተቀዱ ወይም የተገለበጡ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ለመገመት ይቻላል::

'ተራማጅ' ነን፤ፀረአድሃሪ ነን፤የሰፊው ሕዝብ ቤዛ ነን፤ ኢትዮጵያንና ሰፊውን ሕዝብ ለማስቀደም መስዋእት ለመሆን መጣን፤ ወዘተ. በማለት እምቢልታቸውን ሲነፉ የሰነበቱት ጥቂት ቢረኞች መኮንኖች ሰሞኑን ባወጡአቸው ሶስት ህጎች እውነተኛ መልካቸውን:አስከፊውን ጭንጉት ገፃቸውን ገልፀዋል::እንዲህ አድርጎም ራስን በገዛ እጅ ማጋለጥ የለም::

በልዩ ልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 8/1967 በምእራፍ 1 ና 5 የተዘረዘረት ድንጋጌዎች ተራማጅ የሕዝብ ወገኖችንና ሰፊውን ሕዝብ ሰንገው ፀጥ ለማስደረግ የታሰቡ ናቸው:: የሰፊውን ሕዝብ መሰረታዊ ሰብዊና ብሄራዊ መብቶችና ነፃነቶች በፍፁም ይደመስሳሉ:: ስልጣን ኮርቻ ላይ ፊጥ ያሉት እፍኝ የማይሞሉት ቢረኞች የሚሉትን ፍሬከርስኪ:የሚያቀርቡትን ምስቅልቅል ሁሉ ያለአንዳች ቅሬታና ትችት አሜን ብለን እንድንቀበል ሊያደርጉን የታቀዱ ናቸው::

'በመንግስትና በርእሰብሄሩ/ቢረኞቹ/ ላይ የሚሰሩ ወንጀሎች' በሚለው ርእስ ውስጥ የተዘረዘሩት ወንጀሎች በቀጥታና በዘወርዋራ:በልዩ ልዩ መንገድ ወይም ዘዴ ሕዝቡን የቀሰቀሰ:በመንግስቱ ላይ እንዲነሳ ያደረገ:የአገርን ነፃነትና አንድነትና የጉዳ፤ ርእሰብሄሩን /ቢረኞቹን/:ቤተሰቦቻቸውን የነካ:እንቅፋት የሆነባቸው:የተቃወማቸው ወዘተ. በጽኑ እስራትና በሞት ይቀጣል ይላል:: የነገሩ አስከፊነት ይህ ብቻ አይደለም፤ እነዚህ የተመለከቱት የህጉ ቃላት እንደተፈለገ ለመተርጎም የሚያስችሉ:አንዳች ነገር ያልሰራውን ንፁህ አገርወዳድ ሁሉ እንጠርጠስ ሊያስገቡ የሚችሉ መሆናቸው ነው:: ቢረኞቹና የመረጡአቸው ቱልቱላ ዳኞች የማይወዱትን:የማያጉነበስላቸውን:እንደጣእት የማያመልካቸውን ሁሉ ሊገድሉት ይችላሉ:: እንደነአለቃ ፈጠነ:እንደነበቀለ አናሲሞስ:እንደነሻምበልባሻ ገብረፃድቅ ተወልደና እንደብዙዎቹ በሃይለስላሴ ፋሽስታዊ መንግስት ኢሰብአዊ ስቃይና ፍዳ እንደተቀበሉት:ዛሬም ይህ አሰቃቂ ሁኔታ ተመልሶ በመምጣት ላይ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ብሎ ስልጣኑን በያዙት ሰዎች አካባቢ ሲወራ የነበረው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የተፈለገው ይበልጡኑ ለቀድሞ ባለስልጣኖች መፋረጃና መቅጫ ነው:: ምእራፍ 2 እና 3 የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ሙልጥ አድርገው ያራቆቱትን የቀድሞ ባለስልጣናችን ስለሚመለከቱ ወንጀለኞች ይዘረዝራል:: እነዚህ ባገሪቱና በሕዝቡ ላይ ለሃምሳ አመታት ያህል በአምባገነንነት ሲፈነጩበት እንደመቆየታቸው መጠን ከፍ ያለ ቅጣት የሚገባቸው ሲሆን ህጉ ይህን ያህልም ከባድ ቅጣት አላመለከተላቸውም::/በ14/3/67 የተፈፀመው የ60 ሰዎች ግድያ ከህጉ ውጭ የተከናወነ ነው::/ በምእራፍ 3 አንቀጽ 27 በሕዝብ ላይ ከባድ ችግር/እንደአሁኑ ድርቅ/ ሲመጣ በቸልተኛነት ወይም አውቆ ዝም ያለ እንደሆነ ከ10 አመት እስከእድሜ ልክ፤ ሆነ ብሎ ችግሩ እንዲስፋፋ ያደረገ እንደሆነ ቅጣቱ እስከሞት ድረስ ይሄዳል::እንግዲህ ከፍተኛው ቅጣት ይህ ነው

ከዚህ እንደሚታየው የመንግስቱን ስልጣን ጨብጠው ለመያዝ የሚውተረተሩት ጥቂት 'ምርጥ'መኮንኖች ህጉን ያወጡት በእውነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶች ለመቅጣትና የግፍ ዋጋቸውን ለመክፈል ሳይሆን:የሰፊውን ሕዝብ አለኝታዎች በመደምሰስ ያለተቃውሞና ያለተቀናቃኝ በሰፊው ሕዝብ ትከሻ ላይ አንሰራፍተው በመቆየት ለመዝረፍና ለማስዘረፍ ነው:: የዚህ የፋሽስታዊ ህግ ዋና አላማ ሰፊውን ሕዝብ አፉን ለጉሞ:እጁንና እግሩን ጠፍሮ አስሮ በአገርና በውጭ አገር ከበርቴዎች ለማስበዝበዝ መሆኑ ግልጽ ነው::እንደዚህ አይነት ህግ እንዴት አድርጎ ሌላ አላማ ሊኖረው ይችላል.

በልዩ የጦር ፍርድ ቤትም በኩል አሰማው ያው ነው፤ ለይስሙላ ፍርድ ቤት አቁመናል: በህግና በፍርድ ቤት ነው የተቀጡት እያሉ ተራማጅ የሕዝብ ወገኖችን ለማፈንና ለመፍጀት ነው:: ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሌለው ብቻ አይደለም፤ እርግጥ ይግባኝ መሰረታዊ ሰባዊ መብት ነው፤ መደረር መገፈፍ የለበትም::እዚህም ላይ ድርጊቱ ያው ከላይ እንደተባለው ፋሽስታዊነትን በጉልህ ያሳያል:: በፍርድ ቤቱ በኩል ዋና አሳሳቢና አደገኛ ነገር የዳኞቹ ሁኔታ:በደርጉ/ሴረኞቹ/ የሚሾሙ የሚሸሩ:በትእዛዝ የሚሰሩ ወታደሮች ብቻ መሆናቸው እና የህግ እውቀትና የዳኝነት ስራ ልምድ የሌላቸው መሆናቸው ነው::ከእንደዚህ ያለ ሁኔታ ፍትህ ይቅርና ደህና አስተያየት እንኳን ሊገኝ ይችል ይሆን?ፍፁም አይመስለም:: ከዚህ የሚጠበቀው ፍትህ ሳይሆን ተቃራኒው ነው::

አዋጅ ቁጥር 10 'የሕዝብ ፀጥታ ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ ለመጠበቅ' የሚለው የወታደራዊው መንግስት ፍፁም ፋሽስታዊ ህግ ከደቡብ አፍሪካው የሸርስተር ፀረሕዝብ ህግ ጋር ተመሳሳይነት አለው ብለናል::'የዘጠና ቀን እስራት'ከሚለው የዘረኛው ፋሽስታዊ መንግስት አዋጅ የተቀዳ ነው ለማለት ይቻላል፤ የአምባገነን እስራቱ መነሾ ምክንያትና የጊዜው መጠን አንድ ከመሆናቸውም በላይ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ እንደፈለገ ለማራዘም ይችላል::የደቡብ አፍሪካ ጭፍራ የሆነቸው የኢያን ስሚዝ ሮዴሽያም ልክ እንደዚሁ የሆነ:ከዚያው የተቀዳ ፋሽስታዊ ህግ እንዳላት የታወቀ ነው::

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው የዚህ አይነቱ ህግ በስልጣን ላይ የወጡትን ሕዝቡ ያልተቀበላቸውን:በሰፊው ሕዝብ ፈቃድና ምርጫ ስልጣን ያልተቀዳጁትን ፀረሕዝብ አምባገነኖች ለመጠበቅና ስልጣን ከርቻ ላይ ለማቆየት የሚያገለግል አንድ መሳሪያ ነው::በደቡብ አፍሪካ በሸርሸተር የሚመራው የነጮች ብሄረኛ ቡድን የሶስት ሚልዮን ተኩል ነጮችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲል ከ17 ሚልዮን በላይ የሆኑትን ጥቁሮች ለመጨቆንና ለማስበዝበዝ በተባለው ፋሽስታዊ ህግ ይጠቀማል፤ በሮዴሽያም ኢያን ስሚዝ ከግማሽ ሚልዮን የሚያንሱትን ነጮች በአምስት ሚልዮን ጥቁሮች ትከሻ ላይ አስቀምጦ ለማስበጥበጥ ይጠቀምበታል:: የእኛዎቹ ሴረኞች ደግሞ የውጭና የአገር ከበርቴዎችን ጥቅም ለማካበትና ለመጠበቅ ከኢምፔሪያሊዝም በተቀበሉት ትእዛዝ መሰረት ስልጣን ላይ ለመቆየት የአነሸርሸተርን ህግ ገልብጠው አወጁት::

'የዘጠና ቀኑ እስራት ህግ'አላማ ይህ ሲሆን ይዘቱ ደግሞ ማንንም ሰው በማንኛውም በታና ሰአት ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ እያፈሱ እንደከብት በረት ወህኒ ቤት ውስጥ ማጉር ነው:: ይህን አስቀያሚ ፀረሕዝብ ድርጊት እንዲመራ የታደለው የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ነው፤ ባሁኑ ጊዜ የሲአይኤው ተቀዳሚ ቡችላ ኩሉኔል በላቸው ጀማነህ ነው::ይህ የሃይለስላሴ የመጨቆኛ መሳሪያ እንቀባያሽ የነበረ:የብዙ ንፁሃን አገርወዳዶችን ህይወት ያጠፋ:በሰፊው ሕዝብ ደም የተጠመቀ:ባሁኑ ፋሽስታዊ ህግ ያልተደሰቱትንና ያላጉበደደለትን ማናቸውንም ሰው እንዳሰኘው ይዞ ለሶስት ወር ለማሰርና ጊዜውንም ለሌላ ሶስት ወር ለማራዘም ይችላል::ሶስት ሶስት ወር እያለ ጊዜው በላቸው እስከአሰኘው ድረስ ሊራዘም ይችላል፤ ምንም ገደብ የለውም::

እኔ አንተ እርሱ ወይም እርስዋ ለአገርግዛት ሚኒስትሩ ወይም ለፀጥታው ክፍል ሹም ወይም ለፖሊሱ አዛዥ ያላስደሰተን እንደሆነ:የእነርሱን ፕሮፓጋንዳ እንደገደል ማሚቶ ያላስተጋባን እንደሆነ:እውነተኛ የአገር ፍቅር ስሜት ያሳየን እንደሆነ ተይዘን ከማጎሪያው ውስጥ ልንጣል እንችላለን:: የሶስቱን ወር ስቃይ ከጨረስን በሃላ ሌላ ሶስት ወር ሊጨመርብን ይችላል፤ እንዲህ እያለም ይቀጥላል::ላመል ለቀቅ አድርጉ እንደገና እዚያው ሊመልሰን ይችላል::ይህ ብቻ አይደለም፤ ወደፍርድ ቤት ለመቅረብ አንችልም፤ ለሌላ ባለስልጣን ለማመልከት:አቤት ብለን ጉዳዩ እንዲታይልን ለማስደረግ ፍፁም አንችልም:: የጠበቃ:የፍርድ ቤት መቅረብ:የይግባኝ:የአቤቱታ:ያለንበትን ስፍራ ወይም ሁኔታችንን ለቤተሰባችን የማሳወቅና የስንቅና የጥየቃ መብታችን ሁሉ ተደምስሷል::ሚኒስትሩና ቡችሎቹ ከሰውነት ውጭ አድርገው ሊጫወቱብን ይችላሉ:: የነሂትለር የነሙሶሊኒና የነሸርሸተር ፋሽስታዊ ህግ እንደዚህ ነው::የነመንግስቱ ሃይለማርያም/አዲሱ ሃይለስላሴ/ የነበላቸው ጀማነህ /የገስታፖው አለቃ ሂምለር/ የስራ ውጤት እንደዚህ ያለ ነው::

3. በሰፊው ሕዝብ ዘንድ የፈጠረው ስሜት:

በአጠቃላይ ሕዝቡ በእንደዚህ አይነት ስሜት ተቀበለው ለማለት ጊዜው ገና ነው፣ ሀሊናቢስና ገለባ እንደሆኑት ጋዜጠኞቻችን 'በፈገግታና በደስታ' ተቀበለው አንልም::ባድርባይነታቸው:በጭራ ቆይነታቸው:በአስስትነታቸው የታወቁት:ስልጣን ላይ ለወጣ ሁሉ እንደስናር በቀሉ የሚሰግሩት ጋዜጠኞቻችን ከሚያቀርቡት ፍፁም ሃሰትና ፍሬቢስ አስተያየት የእኛው መቶ በመቶ ይለያል:: ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገልለት የቆየውን መብቱንና ነፃነቱን የሚገፍፈውን ፋሽስታዊ ህግ 'እልል ብሎ ይቀበላል' አንልም፣ እንዲያውም በሃዘንና በቁጣ እንደሚመለከተው አንጠራጠርም::እስቲ ለመሆኑ አጥናፍሰገድ የሚባለው እልም ያለ ቀጣፊ ርካሽ አድርባይ ስለፋሽስታዊው ህግ አቀባበል በ14/3/67 በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ርእሰአንቀጽ ውስጥ ያሰፈረውን እንመልከት::

''የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት በቅርቡ ካከናወናቸው ብሄራዊ ተግባራት መካከል 'ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ' አዋጅ ከቀረት ይልቀ ጉላት ነበረው፣ አዋጁ በሕዝብ ዘንድ የመነጋገሪያ ርእስ ሆኖአል፣ ፈላጊውም በመብዛቱ አዋጁ የወጣበት ነጋሪት ጋዜጣ 55 ሳንቲም ብቻ መሸጥ ሲገባው እስከአንድ ብርአውጥ ተአል፣ ታትሞ የነበረውም ቅጂ በሙሉ በአራት ሰአት ጊዜ ውስጥ ተሸጦ አለቀአል''ይለናል:: ይህ እንኳን ማጋነን እንጂ ብዙ ከፋት ያለው አይመስልም:: አዲሱን 'ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ' በሽሚያ ገዝተው ካነበቡት መካከል አናቱን እንደተረዳ ሰው የደነገጡ እንደነበሩና አብዛኛው ሕዝብ ግን 'ይሁን እስኪ ይሁን'ብሎ እንደተቀበለው ጋዜጠኛው ይነግረናል:: ከቢሮው ሳይወጣ አብዛኛውን ሕዝብ እንዴት እንዳገኘው መጠየቅ ተገቢ ቢሆንም የአብዛኛውን ሕዝብ አስይታ ሲነግረን ደግሞ የአጥናፍሰገድን ህሊናቢስ ቀጣፊነት በደንብ እናያለን::

እንደነዚህ አይነት አስስቶች የሚኖሩት ለሆዳቸው ብቻ ነው:: ትሞታለህ:ትታሰራለህ: ትቀጣለህ:ባሪያ ትሆናለህ:ነፃነትህንና መብትህን ተነጥቀሀል:ተረግጠህ ለጥሰጥ ብለህ መገዛት አለብህ ወዘተ. ሲባል እሰይ ብሎ የሚቀበል ሰው ከወዴት ይገኛል.እንዴት ሊኖር ይችላል. ይህን የመሰለ እልም ያለ ውሸት ለመቀባጠርና ለመፍጠር የሚሸቀዳደሙት ለፍርፋሪ የተሸጡት ህሊናቢሶች ብቻ ናቸው::

አብዛኛው ሕዝ'' በእርግጥ እንዴት እንደተቀበለው ለመናገር አንችልም፣ ፈጥረው ለፍርፋሪ መለመኛ ከሚቀባጥሩት በስተቀር ይህንን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ለመናገር የሚችል ያለ አይመስለንም:: ስለሆነም ሰፊው ሕዝብ በቁጣ በድንጋጤ በብስጭት በመማረር በተካዘ በሃዘን ሊቀበለው እንደሚችል ለመገመት ይቻላል::በራዲዮና በቴሌቪዥን ከተነገረ በሂላ የሰው አቀባበል እንደዚያ ነበረ::ወዳጅ መስሎ ጠላት በወረወረው ጦር ጀርባውን እንደተወጋ ሰው እንደሚሰማው አይጠረጠርም:: ሌላ አይነት ስሜት ሊኖረው የሚችል ደንቆሮ ደደብ:የሰውነት ባህርዩ የሞተና ለገንዘብ የተሸጠ ሆዱ አምላኩ ብቻ ነው ብለን እንገምታለን:: አፍህን ትለጉማለህ:እግርና እጅህን ትታሰራለህ: ትገረፋለህ ትገደላለህ ወዘተ. ሲባል ትበላለህ ትሸማለህ ትሸለማለህ ወዘተ. የተባለውን ያህል የሚደሰት ሰው የለምና ነው::

4. ወርቅ ላበደረ ጠጠር:

ምን በበደለ ነው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በዚህ በፋሽስታዊ ህግ እንዲጠፈር የተደረገው. የሰራው መጥፎ ነገር:ወንጀሉ ምንድነው. ምን በወጣው:ምን በገደደ ይህ መአት ይደርስበታል. የሃይለስላሴን የጭቆናና የብዝበዛ አልጋ አነቃንቆ መሪነቱንና የመንግስቱን ስልጣን ለባለመለዮው ስለአስረከበ በዚህ በፋሽስታዊ ህግ መሰንከል ይገባዋል ወይ. ይህማ ባጉረስኩ ተነከስኩ መሆኑ አይደለም.

ባለፈው የካቲት የፈነዳውና አሁንም በመቀጠል ላይ ያለው ሕዝባዊው የትግል እንቅስቃሴ ለአያሌ ዘመናት ውስጥ ውስጡን ሲብላላና ብልጭ ድርግም ሲል የቆየ ነው:: በመደብ በተከፋፈለ በማናቸውም ህብረተሰብ ውስጥ በጨቋኝና በተጨቋኝ በበዝባዥና በተበዝባዥ መካከል የሚካሄደው የትግል እንቅስቃሴ በኢትዮጵያም ሲካሄድ ለመቆየቱ አንዳንድ ሁለት የለውም::

ባለፈው የካቲት ይህ ትግል ሲፈነዳና ቋያው አገሪቱን ከዳር እስከዳር ሲያጥለቀለቃት የሰፊው ጭቁንና ተበዝባዥ ሕዝብ ወገንና ፍላጭ ቀራጭ የሆነው ወታደርም በትግሉ ውስጥ ተሰለፈ ካንዴ ሁለቴ ወጣ ገባ ቢልም የሰፊው ተበዝባዥ ሕዝብ ትግል ሊገታ ባለመቻሉና እየገፋ በመምጣቱ ዋና ዋናዎቹ ግፈኞች ከነአለቃቸው ከስልጣን እንዲወገዱ ተደረገ::ይህ በሰፊው ሕዝብና በወታደሩ በህብረት የተካሄደ ትግል ሲሆን ዋናው አንቀሳቃሽ ሕዝቡ ነው::

ተራማጅ የሰፊው ሕዝብ ወገኖችም በግንባር ቀደምነት ከወታደሩ ጉን ሆነው:እጅ ለእጅ ተያይዘው አይዞህ አለንልህ:በዚህ በኩል በለው፤ ይህንን ለጊዜው አትንካው፤ የሚያዋጣው መንገድ ይህ ነው፤ ይህን አስቀድም፤ ያንን አስከትል ወዘተ. እየተባባሉ የትግሉን አቅጣጫ ሲያመለክቱ አብረው መጡ:: ከመስከረም ሁለት በሗላ አንዳንድ ሴረኞችና ስልጣን ጠማሾች ወታደራዊ መንግስት አቋቁመው ስልጣን ቢይዙም ነገሩ እንደማያዋጣና አሁን ባለንበት የታሪክ ወቅት:ሕዝቡ ዴሞክራሲ በሚጠይቅበት ጊዜ ወታደራዊ መንግስት ማቋቋሙ ትክክል አለመሆኑን፤ ሕዝቡም ለብዙ ዘመናት አፍኖ ከያዘው ልጓም ተላቅቆ በትክክል ፍላጐቱን ለመግለጥ መብቱና ነፃነቱ እንዲመለስለት፤ የተያዘውም አገባብ በጣም አደገኛ:ምርጫውም ስህተተኛ ስለሆነ እንዲለወጥ ከመወትወትና አስተያየታቸውን ከመሰንዘር አልተቆጠቡም::

ለዚህ ጥረታቸው:ለዚህ ትግላቸው የተሰጠው መልስ ሌላ ነው፤ የውጭ እጅ:የጠላት መሳሪያ:የቀድሞዎቹ ባለስልጣኖች ቅሪቶች:የሃይለስላሴ ርዝራዦች:አድሃሪያዎች ወዘተ. ተባሉ::እነዚህን ማጥፋት ነው፤ ያለማወላወል ከባድ እርምጃ ልንወስድባቸው ያስፈልጋል የሚል ዛቻ:ማስፈራራት ማጥላላትና ስም ማጥፋት ብቻ ነበር መልሳቸው::ሰፊው ሕዝብ ግን በዚህ በጥቂት ሴረኞች ተንኮል አልተወናበደም፤ አልደነገጠም፤ በሚችለዉና በሚመቸው መንገድ ትግሉን በመቀጠል ላይ ነው:: ተራማጆችም ከሰፊው ሕዝብ ጉን በመሰለፍ ትግሉን በማንቀሳቀስ ላይ ናቸው:: ይህን እስከምን ጊዜም ቢሆን ይቀጥላሉ፤ ከቶ አንዲት ስንዝር እንኳን ወደሗላ አይሉም::

ታዲያ የሚገርመው ሰፊው ሕዝብ የባላባታዊውን ስርአተማህበር ለብዙ ዘመናት ሲቋቋመው ቆይቶ ባለፈው የካቲት ከስሩ አነቃንቆት ስልጣኑን ከሰፊው ወታደር ጋር ለመያዝ ሲዘጋጅ ከመገለሎም በላይ ስንት ሬሳ ቀብሮ:አጥንቱን ከስክሶ:ደሙን አፍስሶ እዚህ ከደረሰ በሗላ ይህን በመሰለ ፋሽስታዊ ህግ መዘብተቡ ነው:: ነገሩ ወርቅ ላበደረ ጠጠር:እህል ላበደረ አፈር እንደመመለስ ነው::የዚህ ፋሽስታዊ ህግ መታወጅ የክህደት መጨረሻ:ይህ ነው የማይባል ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት ነው::ስለሆነም ትግሉን ከማፋፋም በስተቀር ከቶ አያቆመውም::

5. ጭቁናንና ብዝበዛን የማስወገድ መብት:

ሰው የተፈጠረው ወይም ባለው መልክ ወደዚህ አለም የመጣው በነፃነት ነው፤ ያለአንዳች የጭቁና ሰንሰለት ሙሉ ነፃ ሆኖ ነው የተወለደው፤ ጥቂት የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚጭኑበትን የጭቁና ቀንበር መቋቋም:ሰባብሮ ማስወገድ ዋና መብቱ ነው::

ይህ መሰረታዊ መብት በሰለጠኑት አገሮችና በተባበሩት መንግስታት የሰው ልጅ መሰረታውያን መብቶች ውስጥ በደንብ ተመልክቶአል::ማንም ሰው ወይም ሕዝብ በገዥዎቹ የሚደረግበትን ጭቁናና ብዝበዛ መቃወምና መቋቋም:ታግሎ አንኮትኩቶ መጣል ይችላል::

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከተውን ፋሽስታዊ የህግ ቀንበር አልቀበልም:አልሸከምም፤ እምቢ አሻፈረኝ አልጨቆንም፤ በማለት መቋቋም የእኛ መብትና ግዴታም ጭምር ነው:: ይህ የታወቀና የተረጋገጠ ሰባዊ መብታችን እንደመሆኑ የማስከበሩና ስራ ላይ የማዋሉ ጉዳይ የእኛ ተግባር ነው::በጥቂቶቹ ሴረኞች የሚመራው ወታደራዊ መንግስት የፈለገውን ሊያደርገን:እንደእቃ ወዲያ ወዲህ ሊያዝረን:እንደከብት ያሻውን ሊጭነን:ወደፈለገው አቅጣጫ ሊወስደን ወይም ሊመራን እንዴት ይቻላል? ሰባዊ መብታችን፣ በመገረፍ ከሰውነት ውጭ ወደቁሳቁስነትና ወደእንስሳት ደረጃ ሊለውጠን ሲነሳ በአንድነት ተነስተን መቋቋሙና ሁኔታውን መለወጡ የእኛ ቀዳሚ ግዴታ ነው::

የጭቁናንና የብዝበዛን ቀንበር የመቋቋምና የማስወገድ መብት ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የተያያዘና በአለም መንግስታትም ዘንድ በደንብ ታውቆ የተከበረ ነው፤ ይህ መብት ከሰውነት ጋር የተያያዘና የማይለይ ነው:: ከዚሁ ጋር የተሳሰሩና ከእርሱ የሚመነጩ ሌሎች መሰረታዊ ሰባዊ መብ

ቶች እንደአሉ የታወቀ ነው:: አብዛኛው የሚፈልገውን መንግስት ማቋቋምና የመንግስቱ በሕዝብ ቁጥጥር ስር መሆን: የንግግር የጽሁፍ የማህበር ስራ የማግኘት የደህንነት ወዘተ. መብቶችና ነፃነቶች እንደዚሁም ሌሎች አሉ:: እነዚህን መሰረታዊ መብቶች የሚገፍፍ የሚደመስስ የሚቀንስ የሚያሳጣ አምባገነን ሲነሳ በሃይል መቋቋምና ማስወገድ ታላቅ ክብር ያለው ድርጊት ነው::

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከዚህ በላይ ከፍ ብለን እንዳመለከትነው ፋሽስታዊ የመንግስት ስርአቶች በዚች አለማችን በየጊዜው ብቅ ብቅ ብለዋል:: እነቤኒቶ ሙሶሉኒ:እነአዶልፍ ሂትለር: እነሳላዛር:አሁንም ደግሞ እነፒኖሽተርና እነሶሞዛ ፋሽዝምን ለማንገስ: የሕዝቡን መብቶች ለመደምሰስና በአምባገነንነት እንሰራፋት ለመግዛት ተነስተው ነበር::መጨረሻቸው ግን ምን እንደሆነና ምን ሊሆንም እንደሚችል አስቀድሞ የታወቀ ነው::የሰፊው ሕዝብ ሃይል ደምስሶ ከታሪክ ቆሻሻ ስር ቀብሮአቸዋል፤ የቀሩትንም ይቀብራቸዋል፤ ስፍራቸው እዚያ ነውና:: የእኛዎቹም ፋሽስቶች ከዚያ እንደማያመልጡ ባይታለም የተፈታ ነው:: <u>የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይህን ታሪካዊ ግዴታውን ለማስወገድ ትግሉን በማፋፋም ላይ መሆኑ አይነተኛው የጊዜው ሁኔታ ነው::</u>

6. <u>የሰፊው ሕዝብ የትግል እንቅስቃሴ አገጣጢ</u>:

ባለፈው ቁጥር ጋዜጣችን/14/ እንደተመለከተው የሰፊው ሕዝብ ትግል በገጠርና በከተማ ተፋፋም ላይ ነው:: የትግሉ እንቅስቃሴ ወደከፍተኛ ደረጃ:ወደአዲስ ምእራፍ በመሸጋገር ላይ ነው::

በገጠር ጭሰኛው ገበሬ:መሬትአራሹን በመከተል ባለመሬቱን ዘር በል:ላንተ አርቦ ሲቦ እኩል ማፍሰስ ቀርቶአል፤ መሬቱ ያራሹ ነው፤ የገበሬ ላብ ፍሬ መበዝበዝ ቀርቶአል፤ ከሃይለ ስላሴ ባላባታዊ ስርአት ጋር ወደሞአል፤ አልቆአል ደቆአል ተቀብሮአል፤ እርምህን አሳወጣህ እንደሆነ ይሸውልህ ተረዳው፤ ሁለተኛ እዚህ እንዳትደርስ፤ ግንኙነታችን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ይሁን እንጂ የጭሰኛና የባለመሬት: የበላይና የበታች ግንኙነት ከዛሬ ወዲያ እንዲንቀጥል አንሻም:: ወዳጄ:ይህን ከተቀበልክ መልካም: ያለበለዚያ ደማችን ይፈስሳል እንጂ አንዲት ቁና አንዲት ሳንቲም አታገኝም::ጭሰኛው ይህንንና የመሳሰሉትን በማለት የሚያርሰውን መሬት እጅ አግብቶ በብዙ ስፍራ የመሬቱ ባለቤት ሆኖአል::

ባለመሬትም:ክንዴን ሳልንተራስ መሬቴን ማንም ሊነካ አይችልም፤ መሬቴን አስረክቤ ነገ አፈር ገፊ:ተራ ገበሬ ልሆን:በሬ ጠምጄ ላርስ:ላርም ላጭድ ልወቃ ላግዝ! ይህንንስ ለጠላቴም አያድርገው!ሙቼ ለዚህ ተፈጠርኩና!ይህ ከመድረሱ በፊት ሞቼ መቀበሬ ይሻለኛል ወዘተ. ስማለት በበኩሉ ይበሳጫል:ይደነፋል ይፎከራል ይዘጋጃል::

ጭሰኛና ባለመሬት የእርስበርስ የመደብ ጠርነት ከጀመረ ቆይተዋል፤ ጠርነቱ እየከረረና እየአደገ በመሄድ ላይ ነው:: ሁለቱም ቅርሳቸውን መሳሪያ በመግዛት ያጠራሉ:: መሳሪያውም በዚሁ ምክንያት ያለመጠን እየተወደደ በመሄድ ላይ ነው::ከአመት በፊት አምስትና ስድስት መቶ ብር ያወጣ የነበረው ጓንዴ/ዲምትፍር/ ዛሬ ከሁለት ሺ ብር በላይ ማውጣቱ በይፋ ይነገራል፤ እነሱም ዋንግ አይነሱ! ነገሩ ይህ ብቻ አይደለም:: ልዩ ልዩ መሳሪያዎች ዛሬ ከውጭ አገር በመግባት ላይ ናቸው::ይህም ሆኖ የሕዝቡን ፍላጎት አላረካውም፤ ገበያው በሃይል ደርቶአል:: ይህ ሁሉ ዝግጅት በመቀጣጠል ላይ ላለው የመደብ ጠርነት መሆኑ አንድና ሁለት ያለው አይመስለንም::

ባለፈው ሳምንት እንዳመለከትነውም የተማሪዎችና የምሁራን በሰፊው ሕዝብ ትግል ውስጥ በቀጥታ ለመሳተፍ ወደገጠር መሄድ ከዚህ በላይ የተገለጠውን በጭሰኛና በባለብዙ መሬቶች መካከል በመካሄድ ላይ ያለውን ጠርነት ወደከፍተኛ ደረጃ በመለወጥ ላይ ነው:: ይህ ዛሬ በሰሜን በምስራቅ በደቡብ በምእራብ በሁሉም ስፍራ በተለያዩ ደረጃዎችና መልኮች በመካሄድ ላይ ነው::

በጥቂት 'ምርጥ' መኮንኖች የሚመራው ወታደራዊ መንግስት የተወናበደና የተመሰቃቀለ ፋሽስታዊ ድንብርብርና በደርጉ ውስጥ ያለው የእርስበርስ መበላላት ለሁኔታው እየተባባሰና እየተፋፋመ መሄድ ዋና ምክንያት ነው ለማለት ያስደፍራል:: ለዚህ ሁሉ ሃላፊና ተጠያቂዎቹ በስልጣን ኮርቻ ላይ ሆነው የሚያወናብዱት ጥቂት ዳተኛ መኮንኖችና አጫፋሪዎቻቸው ናቸው:: የከተማውንም ሕዝብ በፋሽስታዊ ህጋቸውና ደብደባቸው ጭጭ ለማድረግ የሚያደርጉት ሙከራ ከምንም ሊያደርሳቸው

እንደማይችል እሙን ነው::በዚህ አገጣጣ በአጣ ምስቅልቅል ድርጊታቸው አንድ እውነት ነገር ቢኖር የገዛ መቃብራቸውን የሚቆፍሩ መሆናቸው ነው:: ሰራተኛ ነጋዴ ባለእጅ ወታደር መምህር ተማሪ ምሁር ሰራአጥ እነዚህ ሁሉ ከተሜያቸም የሕዝባዊውን ትግል እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ ዘዴና መልክ ወደፊት ከማራመድ አልቦዘኑም፣ ትግላቸውን በመቀጠልና በማፋፋም ላይ ናቸው:: ሁኔታው በሚፈቅዱለት መልክና ስርአት ተግሉ ወደፊት ከመራመድ ጋብ አላለም፣ አይልምም::

በአገሪቱዋ በመላ የትግሉ ቋያ በሃይል መንደድ ጀምሮአል፣ በከተማም በገጠርም የመደብ ጦርነት በመፋፋም ላይ ነው:: ሰፊው ሕዝብ በቆራጥነት ትግሉን ከዚህ ላይ ሲያደርሰው፣ ትግሉም ነገድና ብሄር ሳይለይ የመደብን አንድነት አጉልቶ ሲያመለክት በድርጅት በኩል ወደሗላ የቀረ መሆኑ አያከራክርም:: ሰፊው ሕዝብ አጠቃላይና ጠንካራ የትግል ድርጅት ገና አልፈጠረም:: በየአገጣጠሙ የሚካሄደውን የመደብ ጦርነት መልክ የሚያስይዝና የሚያቀናብር:ስልቱንና ዘዴውን የሚቀይስና ወደአዲሱ አይነት የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሚመራ ጠንካራና አጠቃላይ የትግል ድርጅት ከማናቸውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ አስፈላጊ ነው::

ከትግሉ ቋያ ውስጥ ገብቶ የተማገደው ሰፊ ሕዝብ ዛሬ ዋናው ጥሪው:ድርጅት:ጠንካራ ድርጅት:ሁሉን የሚያጠቃልል ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት ነው::ይህ ጥሪ ለማን ነው? ሰፊው ሕዝብ የድርጅት ያለህ:የጠንካራ አጠቃላይ የትግል ድርጅት ያለህ እያለ የሚጮኸው ለማ ነው? ይህ ጥሪ በመጀመሪያ የሚመለከተው ቀደም ብለው የሰፊውን ሕዝብ ወገን በመምረጥ በትግሉ ሜዳ የገቡትን ተራማጆች ነው:: የእነዚህ የሕዝብ ወገን ተራማጆች ታሪካዊ ተግባር ባሁኑ ወቅት ሰፊው ሕዝብ የሚጮህለትን:የሚወተውትለትን ጠንካራና አጠቃላይ ሰፊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት መፍጠርና ትግሉን ወደድል መምራት ነው:: ይህ ነው የጊዜው አቢይ ጥሪ::

አወናባጆቹና አጭበርባሪዎቹ አፍኝ የማይቃሉት ሰረኛ መኮንኖች በሰፊው ሕዝብ ጫንቃ ላይ ቀንበራቸውን ለመጫንና በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርጉትንም ፋሽስታዊ ጥረት ለማክሸፍና ስልጣኑን ለባለቤቱ ለሰፊው ሕዝብ ለመመለስ የሚቻለው በመደራጀትና ትግሉን በቆራጥነት ወደፊት በመምራት ነው::

ድርጅት ሃይል ነው እየተባለ ብዙ ጊዜ መወሳቱ ብቻ በቂ አይደለም:: ድርጅት ሃይል መሆኑ በብዙ አገሮች በተግባር የታየ በስራ ላይ የዋለ ቅንጣት ያህል እንኳ የማያጠራጥር እውነት ነው:: ሰፊው ሕዝብ የሚጮህለትን ጠንካራና አጠቃላይ የትግል ድርጅት ቶሎ ብሎ መፍጠር በግብር ማሳየት ያስፈልጋል::የሰፊውን ሕዝብ ጥሪ መመለሻ ሰአት አሁን ነው:: ምንም አይነት ሌላ ምርጫ ባሁኑ ጊዜ የለንም:: ታሪካዊ ግዴታችንንም ቶሎ ብለን ካልተቀበልንና ካልፈፀምን:ከእጅ አይሻል ደማ:የአፍ እንጂ የተግባር ሰዎች አለመሆናችንን አስመስክረን ከታሪክ ቆሻሻዎች ጋር አብረን ከመቃጠል አናመልጥም:: ይህን ጥሪ ልብ አድርገን ተገንዝበን በፍጥነት እንድንመልሰው ያስፈልጋል::

ላዲሱ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እንደርጅ፣
ሰፊውን ሕዝብ እናደራጅ፣አጠቃላይና ጠን
ካራ ሰፊ የትግል ድርጅት ለመመስረት
ቆርጠን እንነሳ::
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::